# <u>የፖለቲካ ፔንዱለም</u>

**<u>ከ፡ ነሲቡ ስብሐት</u> Verginia USA** ነሐሴ 14 ቀን 2023 ዓ.ም. (August 20 2023)

nhsibhat@gmail.com, (703)3004302

የሀገራችን የፖለቲካ ተዋንያን አንዳንዴ ይገርሙኛል። ለዓላማ ሳይሆን ለዝና ድፍረታቸው፣ ለጽናት ሳይሆን ለመገለባበጥ ችሎታቸው፣ ምላጭ ምላሳቸው፣ የንቀት አንደበታቸው፣ መሰሪ ጉዟቸው፣ እንደሸማኔ ድር ማዳወሪያ ከወዲያ ወዲህ ለመወርወር ፍጥነታቸው፣ እንደ ፔንዱለም ዥዋዥዌ ጨዋታቸው ሌላም ሌላ ሊባልላቸው የሚመጥኑና ሲያንሳቸው ነው የሚባሉ የፓርቲ እና ድርጅት ቱሪስቶች በርካታ ናቸው።

በሞቀበት መታየት የሚፈልጉ፣ ሁሌም የመጀመሪያ ለመሆን ሩጫቸው፣ የሚጠይቋቸው ላይ ማፍጠጣቸው፣ የሚተቿቸውን ማቀጨጫቸው፣ በሚመክሯቸው ማፌዛቸው ሳይቀር ስለ ሕዝብ ተናጋሪ "ከእኛ በላይ ላሳር"፣ ስለ ሀገር "እኛ ብቻ"፣ አለን የሚሉትን ተመክሮ አጣጥመው የበሉ፣ ፈጥነው ለማጨብጨብ ቀዳሚዎች፣ አልመች ሲላቸው ተቃዋሚዎች፣ ትግል ከዓላማ ይልቅ ከነሱ ምኞትና ድሎት አንጻር ተመልካቾች በበዙበት የፖለቲካ መንደር እንዴት ተደርጎ የሀገርና የሕዝብ ችግር ይፈታ? ከሚፈለግበትስ ግብ እንዴት ይድረስ?

በትንሹ ከዘመነ ወያኔ/ህወሓት አገዛዝ 1983 ዓ.ም. ወዲህ ተፈጥረው የከሰሙ ድርጅቶች ወይም ፓርቲዎች ብናይ ለምን እንዳጀማመራቸው አልቀጠሉም? ብንል መልሱ አንድና አጭር ብቻ ነው። ትግላቸው ዓላማ ስለሌለው፣ ግባቸውን ስለማያውቁ ነው ማለት ይቻላል።

ከ1997 አካባቢን ብንቃኝ ቅንጅት፣ ሕብረት ብሎ የተጀመረው የዘመነ ወያኔ የምርጫ ተንቀሳቃሾች እየተበጣጠሱ አንዴ ቅንጅት ኢንተርናሽናል፣ ቅንጅት ምናምን ሲሉን ሕብረትም ሸንጎ ብሎ ስም ሲቀይር ምንም ጠብ አልል ሲላቸው ዛሬ ሁሉም የሉም ሳይሆን በሌላ ስም ይፈጠራሉ ወይም በተፈጠሩት ውስጥ ይሰገሰጋሉ።

አንዳንዶች የዳያስፖራ ገንዘብ ጥሟቸዋል። እስቲ እራሳችሁን ጠይቁ በቅንጅትና ሕብረት ጊዜ ስንት ገንዘብ ተሰበሰበ? ለኢሳት፣ ለግንቦት 7፣ ለአርበኞች ግንቦት 7 እየተባለ የተሰበሰበ ገንዘብ ትግሉን የት አደረሰ?

ለትውስታ ያህል ይህን ካነሳሁ በቀጣይነት የዛሬ 5 ዓመት ዶር ዐብይ አሕመድ በጥገናዊ ለውጥ ስም ብቅ ሲል በወያኔ/ህወሓት ዘረኛ አገዛዝ እጅግ ከመማረርና ሀገርና ሕዝብ ካንዣበበባቸው የመበታተን አደጋ ለመታደግ ሁሉም እስከ ችግሩ ድጋፉን ሲቸር ያንዳንዶች ግን ማሽቃበጥና ጭራ መቁላት ለትዬ ለኔ ያህል ጦዞ ነበር። በዶር ዐቢይ የ"መደመር" ዲስኩር ከባለቤቱ በላይ አራጋቢዎች ሌሎች ነበሩ፣ ሌላ መስማትም ሆነ ማየት አጢያት፣ ውግዝ ከማሪዮስ ተደርጎ ተወገዘ። የሀገሪቷ መሠረታዊ ችግር ተዘንግቶ በዐብይ የስልጣን ኮርቻ ውስጥ ለመደባለቅ ዋና ነን ባዮች ዝላያቸው ጨመረ፣ ተጀምሮ የነበረን የጋራ ትብብር ደፍጥጠው ሁሉም ሩጫ ወደ ዐብይ አደረጉ። እሽቅድምድሙ ጦፈ።

በድርጅት ደረጃ እንደ ግንቦት 7 ዓይነቱ ስሙን ኢዜማ ብሎ ዋናው የዐብይ አጨብጫቢ በመሆን የደርጉን መኢሶን ታሪክ ደጋሚነቱን አሳየ። ኢሳት የግንቦት 7 ተለጣፊ እንደነበር ሲነገራቸው ይንጫጩ የነበሩ ሁሉ ግንቦት 7 ኢሳትን ከማበጣበጥ አልፎ እንዲበተን አደረገው። "ኢሳት የሕዝብ ዓይንና ጆሮ" ተብሎ በዳያስፖራ የማያቋርጥ መዋጮና እገዛ ጫፍ የደረሰው የዜና አውታር ተሸመደመደ፣ ተኮላሸ። ይህ ሁሉ ድርጊት አየር ላይ የሰቀልነው የግንቦት 7 ድርጅት አመራር አንድ ግለሰብና ግብረአበሮቹ ነበሩ። በቀዳሚነት ድርጅቱ የአንድ ግለሰብ ንብረት ነበርና ለዐብይ የማያስፈልጉ ያላቸውን በተናቸው፣ ከራሱ የድርጅት አባላት አልፎ በኢዜማ ስም የደባለቃቸውን በመዋጥ ደብዛቸውን አጠፋቸው። ለራሱ ግን ይፈልግ የነበረው በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ቅርቃር መግባት ነበርና የዝላዩ ውጤት የሚንስትርነት ቦታ አስገኘለት። ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ ለትምህርት ሚኒስትርነት በላይ የሚመጥን ችሎታና ዕውቀት ቢኖረውም ግቡ፣ ዓላማው ግን ቀደም ሲል በእነ መለስ ዘመን አግኝቶ ያጣውን ቦታ ማግኘት ነበርና "እንደተመኘኋት አገኘኋት" ብሎ ዘው ማለት ብቻ ሳይሆን በቀጣይነትም ያደረጋቸውና የሚያደርጋቸው ተግባራት የማንነቱ መገለጫዎች ነበሩ፤ ናቸው።

ይህ እንግዲህ ከ1997 ዓ.ም. ጀምሮ በርካታ ገንዘብና የሰው ኃይል የፈሰሰበት የግንቦት 7 ግብ በዚህ ሲቋጭ በዚህ ሂደት የሌሎችን ስም መግለጽ ባያስፈልገኝም አንባቢ እራሱ እነማን ነበሩ? ብሎ ይጨምርበት።

የዚህ ጽሁፌ ዋና ጭብጥ ሁሉንም ባላነሳ አንዳንዶች ልክ እንደ ፔንዱለም የትግል ዥዋዥዌ ሲጫወቱ ይስተዋላሉ። ከዘረኛው ዐብይ አሕመድ ጋር ሲሞዳሞዱ ከርመውና አድረው ሀገር አጣብቂኝ ውስጥ ስትገባ ደግሞ ዘለው መጥተው የተለመደ ማደንቆራቸውን ሊደግሙልን ይፈልጋሉ። አዎ! በሠሩት ሥራ ተሰምቷቸው ጥለው ከሀገር የወጡ ድምጻቸውን አጥፍተው አርፈው የተቀመጡ ወይም ርጋታን የተላበሱ ቢኖሩም አንዳንድ ደፋሮች ደግሞ አሁንም እንደገና ስለ ትግልና ስለ ዐብይ ብልሹ አስተዳደር ሰባኪና አዋቂ እኛ ስለሆንን ለትግል መጣን ሲሉን ኸረባካችሁ ይህን ያህል አትናቁን ሊባሉ ይገባቸዋል።

አጥንቱን እየከሰከሰ ደሙን እያፈሰሰ ለህልውናውና ለኢትዮጵያ ሀገሩ አንድነት እየተዋደቀ ያለውን አማራ ሲፈናቀል፣ ሲታሰር፣ በተለያየ ቦታና ጊዜ (ቡራዩ፣ ሻሸመኔ፣ አጣዬ፣ ወለጋ፣...) ሲጨፈጨፍ አድፍጠው ተመልክተው አሁን ትግሉ ሲግል ሲጎመራ እንደገና ዥዋዥዌአቸውን አሳምረው በመምጣት አለን ሲሉ ድፍረታቸው ሊነገራቸው ይገባል።

እውነት እንነጋገር ከተባለ ሀገራችን የታጋይም፣ ያታጋይም ደሀ አይደለችም። ከአሁኑ ከአዲሱ ትውልድ እንኳ በርካታ ቆራጥ ልጆች አሏት። ግና “ከእኛ በላይ ላሳር” ብለው በኢጎ የተወጠሩ ፖለቲከኞቻችን መች አስጠግተዋቸው። ቢያስጠጉም እነሱ በሚሉት ላይ መከራከር አይደለም አሜን ብለው የሚያስተጋቡላቸውን የገደል ማሚቶ መራጮች ናቸውና ማ ሊያስጠጋቸው። የፖለቲካ ልክፍት የተዋሃዳቸው ትላንታም፣ ዛሬም በነበረ ድርጅት፣ ሕብረት፣ ግንባር ሌላም ስም እንስጠው ውስጥ እንደፖለቲካ ፓርቲ ቱሪስት ዘው ብለው ሁሉም ጋ እነሱ ብቻ ሊታዩ ፈላጊዎች ትግሉን መጉዳት ብቻ ሳይሆን እያሽመደመዱ ናቸውና ሊነገራቸው ይገባል። ድፍረታችሁን ምናለ ለትግሉ ብታደርጉት ሊባሉ ይገባል።

በተደጋጋሚ ወደ ውጭው ዓለም ወጥቷል፣ እንደሌሎቻችሁ እዚህ ቁጭ ብሎ በስሙ እየነገደ ገንዘብ መሰብሰብ፣ የመጓጓዥ እየተከፈለለት፣ ሆቴል ተይዞለት፣ ለምግቡ ሳያስብ እየተዋጣ ለኪሱ እየተሰጠው በተጨማሪም አፍቃሪ ወገኖቹ በግልም እየተንከባከቡት ከአንዱ ስቴት ወደ ሌላው ብቻ ሳይሆን ከዩኤስዬ ወደ ደቡብ አፍሪካ፣ አውሮፓ፣ አውስትራሊያ፣ ኤሺያ በጥቅሉ ኢትዮጵያዊ በአለበት የዓለም ዳርቻ ሁሉ እየተሽከረከረ በመኖር ከአንድዬ ልጁና ባለቤቱ ጋር ከሌሎቻችን በበለጠ ተንደላቆ እየኖረ መታገል አቅቶት አይደለም በረሃ ለበረሃ የሚንከራተተው፤ እስክንድር ነጋን ማለቴ ነው።

የኛ የፖለቲካ ፔንዱለሞች ግና ወይ ድምጻቸውን አጥፍተው አርፈው አይቀመጡ የ“አማራ ፋኖ” የጦር ሠፈር ሎንደን ይመስል ለትግል መጥተናል እያሉ ሲፎክሩ ዝም ማለት ለዳግም ድፍረታቸው በር መክፈት ነውና አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ እንኳን በደህና መጡ እያልኩ ግና ምናለ ዝም ብለው ቢቀመጡ እላለሁ።

የተቻሎታዎን ጥረዋል፣ ታግለዋል ግና እስቲ ለሌሎች ላላየናቸው እድል ለመስጠት ይሞክሩ። አይታገሉ አልልም ይታገሉ ግና ዳርዳርታዎን ይግቱት። የታጋይም ሆነ የአመራር ድህነት የለብንም። ስለ ዐብይ/ብልጽግና ማንነት ነጋሪም ሆነ ምስክርነት የምንፈልግበት ጊዜላይ አይደለንም። በየቀኑ ደም እየፈሰሰ አጥንት እየተከሰከሰ የሰው ልጅ እየታረደ ያለው በትንሹ 5 ዓመት “አማከርኩት” በሚሉት ዐብይ አሕመድ አገዛዝ ነውና ለምክሮ ምስጋናውን ከሱ ይውሰዱና ቀደም ሲል በ360 እንደተዘገበውም ወስደዋልና እስቲ እዚህ ያለውን ለቀቅ ያድርጉትና ትንሽ ከራሶ ጋር ይነጋገሩ እላለሁ።

በአርበኞች ግንቦት 7 ተመክሮዎ በኤርትራ በረሃ ከነበሮት የማዋጋት ልምድ ወደ ለንደን ከመጓዝ ይልቅ ወደ ***“አማራ ፋኖ”*** ተቀላቅለው የአዋጊነት ልምዶን ቢያካፍሉ ምን ያህል በተመሰገኑ። እና እባካችሁ ይህች መከራ ላይ ያለች ሀገርና ምስኪኑ ሕዝባችንን እናክብር።

ይህ ጽሁፌ ስም ባልተቅስም ሌሎችም የሚመለከታችሁ እንዳላችሁ ብገምትም ዝምታችሁን እራሱ አከብራለሁ። ቀጣይ ምላሽ የሚሰጥ ካለ ለሌላ ዝርዝር ዝግጁ ነኝ።

በሌላ በኩልም አንዳንድ የሚዲያ ባለቤቶች፣ ጋዜጠኞችና አክቲቪስቶች እንዲሁም የዩትዩብ ለቃቂዎች ለእንደነኚህ ዓይነት እፍረትን አጣጥመው ለሚወዛወዙ ፔንዱለም ፖለቲከኞች የሚዲያ ጊዜ እየሰጣችሁ ባታበሳጩን መልካም ነው እላለሁ።

የ***“አማራ ፋኖ”*** ትግል እያየለ ሲመጣ ከዐብይ/ብልጽግና የፖለቲካ መዋቅርና አስተዳደር ገና የሚከዱና ሀገር ጥለው የሚኮበልሉ ሊኖሩ ይችላሉ። ይህ የ***“አማራ ፋኖ”*** ትግልን ጥንካሬ የሚያሳይ ሂደት ሳይቀዘቅዝ ወደ ድል ይገሰግስ ዘንድ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠይቃል። ማንም በሁለት ቢላዋ ሊበላ መጨረሻው ላይ ሲፈረጥጥ የሚፈለግ አንዱ የትግል ውጤት ቢሆንም በዚህ መልኩ እየመጡ ታጋይና አታጋይ ያጣን ይመስል በየድርጅቱ ውስጥ እንደ ትልቅ ድል እነሱን ለመሰግሰግ መሞከር ትግሉን ከማቀዝቀዝ በቀር የሚፈይደው እንደሌለ ከዚህ በፊት ስዬ ሃብርሃና ገብሩ አሥራትን “ምሩን” እስከመባል የተጨፈረላቸው ሂደት ምን ውጤት እንዳስመዘገበ መለስ ብለን እናስታውስ።

በሌላም በኩል ተንኮል ጎረቤቱ የሆነው የዐብይ አመራርን ተጣላን በማለት ወደ ዲያስፖራው እንዲመጡና ቀዳዳ ካገኙ ሚስጥር በማቀበል ይህን የ***“አማራ ፋኖ”*** እንቅስቃሴ ከምንጩ ለማዳከም ብቻ ሳይሆን ለመምታት እንደሚያቅድ ልምድ ላላችሁ ፖለቲከኞች ነጋሪ የሚያስፈልግ አይመስለኝምና በጥንቃቄ የተፋፋመው የ***“አማራ ፋኖ”*** ፍልሚያ ሌሎችን አቅፎ ጊዜው አጥሮ በድል ይጠናቀቅ ዘንድ እንረባረብ እላለሁ።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!
ፈጣሪ ሀገራችንን ይጠብቃት!!!
ቸር ይግጠመን
ነሲቡ ስብሐት nhsibhat@gmail.com (703) 300 4302
ነሐሴ 14 ቀን 2015 ዓ.ም. (August 20, 2023)